**מדינת ישראל**
**משרד החינוך**
סוג הבחינה: בגרות
מועד הבחינה: קיץ תשע"ט, 2019
**מספר השאלון: 029284**
נספחים: נספח לשאלה 6
נספח לשאלה 7
**תרגום לאמהרית (6)**

# היסטוריה דתי
## לעולים חדשים
### בבתי ספר דתיים

**הוראות לנבחן**

א. משך הבחינה: שעתיים וחצי.

ב. מבנה השאלון ומפתח ההערכה:

בשאלון זה שלושה פרקים.

| | | | |
|---|---|---|---|
| פרק ראשון | (13×3) | — | 39 נקודות |
| פרק שני | (22×1) | — | 22 נקודות |
| פרק שלישי | (13×3) | — | 39 נקודות |
| סה"כ | | — | 100 נקודות |

ג. חומר עזר מותר בשימוש:

מילון עברי-לועזי / לועזי-עברי.

ד. הוראה מיוחדת:

בתשובתך הבא עובדות, אל תסתפק בהערכות כלליות.

כתוב במחברת הבחינה בלבד. רשוֹם "טיוטה" בראש כל עמוד המשמש טיוטה.
כתיבת טיוטה בדפים שאינם במחברת הבחינה עלולה לגרום לפסילת הבחינה.

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**ב ה צ ל ח ה !**

**እስራኤል አገር**
የትምህርት ሚኒስቴር
የፈተናው ዓይነት፦ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና
የፈተናው ጊዜ፦ የ2019 ዓ.ም. የበጋ ፈተና
**የፈተናው ቁጥር፦ 029284**
አባሪዎች፦ አባሪ ለጥያቄ 6
አባሪ ለጥያቄ 7
**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# የሃይማኖት ታሪክ
## ለአዲስ ገቢዎች
### በሃይማኖተኞች ት/ቤቶች ለሚማሩ

**ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች**

א. ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ፦ ሁለት ሰዓት ተኩል።

ב. የፈተናው መዋቅርና ነጥብ አሰጣጥ፦

ይህ ፈተና ሦስት ምዕራፎችን ይዟል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምዕራፍ አንድ | (3x13) | — | 39 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሁለት | (1x22) | — | 22 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሦስት | (3x13) | — | 39 ነጥብ |
| በአጠቃላይ | | — | 100 ነጥብ |

ג. ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ፦

የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

ד. ልዩ መመሪያ፦

በመልስህ ላይ ተጨባጭ እውነታዎችን አሳይ፤ ጠቅለል ባለ መልስ አታብቃ።

በመጠይቁ ደብተር ላይ ብቻ ጻፍ። ለማስቢያ በምትጠቀምበት ገጽ መግቢያ ላይ በሙሉ "טיוטה" ብለህ ጻፍበት።
ከመጠይቁ ደብተር ውጭ በሆነ ወረቀት ማሰቢያ መጻፍ ለፈተናው ውድቅ መሆን ምክንያት ሊሆን ይችላል።

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢሆኑም ለወንድም ለሴትም ተፈታኞች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

# ጥያቄዎቹ

## ምዕራፍ አንድ (39 ነጥብ)

ከ1-5 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ — 13 ነጥብ)

**1.** የዘመናዊ ብሔርተኝነትን (לאומיות המודרנית) ዓላማ **አሳይ/ግለጽ**።

አክራሪ ብሔርተኝነት (לאוּמָנוּת) በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ የተወሰኑ ቡድኖችን ሊጎዳ የሚችለው ለምን እንደሆነ **አብራራ**።

**2.** በይሁዳ ቤን ኤልዔዘር እና በአሮጌው ሠፈራ በነበሩት የአሽከናዚ ማኅበረሰብ መካከል የዕብራይስጥን ቋንቋ ዕለት ዕለት በመጠቀም ጉዳይ ላይ የነበሯቸውን እያንዳንዳቸውን የመከራከሪያ አቋማት **አብራራ**።

ይሁዳ ቤን ኤልዔዘር የዕብራይስጥ ቋንቋን ዕለት ዕለት መጠቀምን ለማሻሻል ያደረገውን አንድ ድርጊት **አቅርብ**።

**3.** በፓለቲካዊ ጽዮናዊነት (הציונות המדינית) እና በተግባራዊ ጽዮናዊነት (הציונות המעשית) መካከል ያለውን ልዩነት **አቅርብ**።

የባልፉር አዋጅ በጽዮናዊያን እንቅስቃሴ ዕይታ አስፈላጊ ስኬት የሆነው ለምን እንደነበር **አብራራ**።

**4.** ለአንደኛው የዓለም ጦርነት መፈንዳት መንስዔዎች የሆኑት ነገሮች በፊትህ አሉ፦ የጦር መሣሪያ ለመታጠቅ ሩጫ (מֵרוץ החימוש)፣ ወደ ኢምፔሪያል ሩጫ (מרוץ האימפריאלי)፣ የኦስትሮ-ሃንጋሪ ልዑል ወራሽን መግደል (רצח יורש העצר האוסטרו־הונגרי)።

አንዱን **ምረጥ** እና የመረጥከው መንስዔ እንዴት ለመጀመሪያው የዓለም ጦርነት መፈንዳት ምክንያት እንደሆነ **አብራራ**።

የመጀመሪያውን የዓለም ጦርነት አንድ መለያ **አቅርብ**።

**5.** የእስራኤል አገር ዓረቦች በፓገማ 1936-1939 (בפרעות תרצ"ו-תרצ"ט) የይሁዳዊያን ሠፈራዎችን በመቃወም ያደረጓቸውን ሁለት ድርጊቶች **ጥቀስ**።

አንድ የሽምቅ ተዋጊ (מחתרת) ድርጅት — *ሀሃጋና (ההגנה)ን* ወይም *ሀኤጼል (האצ"ל)ን* **ምረጥ**።

የመረጥከውን ድርጅት ስም **ጥቀስ** እና በዚህ ወቅት "ምላሽ አለመስጠት" ("הבלגה") ወይም "ምላሽ መስጠት" ("תגובה") በሚለው ክርክር ላይ የነበረውን አቋም **አብራራ**።

/ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል/

## ምዕራፍ ሁለት (22 ነጥብ)

ከ6-7 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱን መልስ።

**6.** שינויים בחיי היהודים בסוף המאה ה־19 ובתחילת המאה ה־20 (በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ እና በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በይሁዳዊያን ሕይወት የመጡ ለውጦች)

**א.** በጥያቄ 6 አባሪ ላይ ከ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያዎች የሆነ ፖስት ካርድ (ደብዳቤ ከፎቶ ጋር) አለ። የኦስትሮ-ሃንጋሪ ይሁዳዊ ቤተሰብ የፋሲካ ምሽት በፖስታው ላይ ይታያል።

የይሁዳዊያንን ልማድን ጠብቆ ማቀየት በፖስት ካርዱ ላይ ካሉት ክፍሎች (רכיבים) በአንዱ መሠረት እንዴት ተግባራዊ እንደሆነ **አብራራ**።

ይሁዳዊ ቤተሰብ ከአጠቃላይ ማኅበረሰቡ ጋር መጣመሩ በፖስት ካርዱ ላይ ካሉት ክፍሎች በአንዱ መሠረት እንዴት ተግባራዊ እንደሆነ **አብራራ**።

(11 ነጥብ)

**ב.** የשהרש"ר הירש'ን "תורה עִם דרך ארץ" ራዕይ **አቅርብ** እና ይህን ሃሳብ እውን ለማድረግ ያደረገውን አንድ ድርጊት **አቅርብ**።

(11 ነጥብ)

**7.** "המזרחי" ו"הפועל המזרחי" ("ሃሚዝራሂ" እና "ሃፖኤል ሃሚዝራሂ")

**א.** ከጽዮናዊያን እንቅስቃሴ ውስጥ "ሃሚዝራሂ" የሚለውን እንቅስቃሴ ለይቶ/ለብቻ የማቋቋሙ ምክንያት ምን እንደሆነ **አቅርብ**።

ጽዮናዊው እንቅስቃሴ ኃይማኖት ከማይጠብቁት (חילונים) ጋር መተባበሩን ራብ ሬይንስ እንዴት ትክክል ነው እንዳሉ **አብራራ**።

(11 ነጥብ)

**ב.** በጥያቄ 7 አባሪ ላይ በ1951 ዓ.ም. የ"ሃፖኤል ሚዝራሂ" የምርጫ አዋጅ የነበረ ማስታወቂያ ቀርቧል። የ"ሃፖኤል ሚዝራሂ"ን "תורה ועבודה" ራእይ **አቅርብ**።

"תורה ועבודה" ከሚለው ጹሑፍ በስተቀር የ"תורה ועבודה" ራዕይ በማስታወቂያ ላይ እንዴት ተግባራዊ እንደሆነ **አብራራ**።

"המרד הקדוש" ተቃውሞ የተነጣጠረባቸው ሁለቱ ቡድኖች እነማን እንደነበሩ **ጥቀስ**።

(11 ነጥብ)

/ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል/

## ምዕራፍ ሦስት (39 ነጥብ)

ከ8-12 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን መልስ (እያንዳንዱ ጥያቄ — 13 ነጥብ)።

**8.** በእስራኤል ላይ ያለ ልማዳዊ ጥላቻ (שנאת ישראל המסורתית) በምን ላይ እንደተመሠረተ **አቅርብ**።
ዘመናዊው ፀረ-ይሁዳዊነት (האנטישמיות המודרנית) በምን ላይ እንደተመሠረተ **አቅርብ**።
ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እስከፈነዳበት (1933-1939) ጊዜ ድረስ ናዚዎች በይሁዳዊያን ላይ የወሰዱትን አንድ ድርጊት **አቅርብ**።

**9.** በ"ሾአ" ወቅት በማጎሪያዎቹ የነበሩት ጁዴራንት መሪዎች የነበረባቸውን አንድ ችግር **አቅርብ**።
ጁዴራንቶቹ የጌቶ ይሁዳዊያንን ሕይወት ለማሻሻል ካደረጓቸው ሙከራዎች ሁለት ምሳሌዎች **ጥቀስ**።

**10.** የሜሪ ሃዒብሪ (מרי העברי) (1945) እንቅስቃሴ እንዲቋቋም ያደረገን አንድ ምክንያት **አቅርብ**።
ይህ እንቅስቃሴ ያደረገውን አንድ ድርጊት **ጥቀስ**።
የሜሪ ሃዒብሪ እንቅስቃሴ (1946) የፈረሰበትን አንድ ምክንያት **አቅርብ**።

**11.** በነጻነቱ ጦርነት የዓረብ አገራት ከእስራኤል ጋር ያለውን ጦርነት ለመጨረስ የተኩስ ማቆም ስምምነት ለመፈራረም (1949) የተስማሙበትን አንድ ምክንያት **አቅርብ**።
የነጻነቱ ጦርነት እና አገርን ማቋቋሙ በዓረብ አገራት በነበሩ ይሁዳዊያን ሕይወት ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንዳደረጉባቸው **አብራራ**።

**12.** በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአሥራ ዘጠኝ ሰባዎቹ እና ሰማንያዎቹ ዓመታት ላይ ይሁዳዊያን ከሶቭዬት ኅብረት እና ከኢትዮጵያ ወደ እስራኤል አገር ገቡ።
የሶቭዬት ኅብረት ይሁዳዊያን ወደ እስራኤል ዓልያ ያደረጉበትን አንድ ምክንያት **አቅርብ** እንዲሁም የኢትዮጵያ ይሁዳዊያን ዓልያ ያደረጉበትን አንድ ምክንያት **አቅርብ**።
በፊትህ ከተማርካቸው ከሶቭዬት ኅብረት የመጡ ሰዎች ስሞች እና ከኢትዮጵያ የመጡ ሰዎች ስሞች ቀርበዋል፦ ዮሴፍ ሜንደሎቪች፣ ናታን ሻራንስኪ፣ ዩሊ ኤድልሽቴይን፣ ኢዳ ኖደል፣ ዮና ቦጋለ፣ ራባን ሞሼ ሰሎሞን፣ ፒኒና ታመኑ እሽቴ።
ከእነዚህ ሰዎች ውስጥ አንዱን **ምረጥ** እና ስሙን **ጥቀስ**። ከመጣበት አገር ያደረጋቸውን እንቅስቃሴዎች (פעילות) ወይም በእስራኤል አገር ያደረጋቸውን እንቅስቃሴዎች **አቅርብ**።

**መልካም ዕድል!**

**בהצלחה!**

መብቱ ለእስራኤል መንግሥት የተጠበቀ ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።
זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך

## የጥያቄ 6 አባሪ — የይሁዳዊያን ፖስት ካርድ (ደብዳቤ ከፎቶ ጋር) በፋሲካ ምሽት (1916)




የኦስትሮ-ሃንጋሪ ቄሳር ፍራንች ዮሴፍ ፎቶ

(http://web.nli.org.il/sites/NLI/English/digitallibrary/Pages/Viewer.aspx?presentorid=NLI_EDU&docid=NNL03_EDU700276018)

## የጥያቄ 7 አባሪ — የምርጫ ማስታወቂያ (1951)




በመገንባት ላይ ላለች አገር መነሻ ኃይማኖታዊ ባህሪይ የተዋጋ
የ"ሃፖኤል ሚዝራሂ" (ታሪክና ተግባር) ዝርዝር

(https://www.palestineposterproject.org/poster/israeli-election-1955-circa)